# ኢዴአፓ-መድህንና የምርጫ አጀንዳ

ሰላማዊ ትግልና ምርጫ ሲነጣጠሉ የማይችሉ ሂደቶች ናቸው፡፡ ምርጫ በሰላማዊ ትግል ወደ ሥልጣን መምጫ መንገድ ነው፡፡ በሰላማዊ ትግል አንዱ ሌላውን በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን ለመያዝና ሲሸነፍም ከሥልጣን ለመውረድ የምርጫ ውድድር ፍትሃዊና ሚዛናዊ መሆን እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ ኢዴአፓ-መድህን በአገራችን ነፃ፣ ፍትሃዊና ሚዛናዊ ምርጫን እውን ለማድረግ ያሉብንን በርካታ ችግሮች በአፅንኦት ይገነዘባል፡፡

ፓርቲያችን እነኝህን ችግሮች የሚረዳበት መንገድ በአጠቃላይ ለአገራችን ባልተቋረጠ ትግል ሂደት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በዘላቂ መሠረት ላይ ለመገንባት ካለው አስተሳሰብ መነሻነት ነው፡፡ የምርጫ ሂደት ለኛ ሕዝብን በቀጥታ በፖለቲካ የምናሳትፍበት፣ ሕዝቡ መብቱን ለማስከበርና ሥልጣኑን ለማሳየት ቀጥተኛ ዕድል የሚያገኝበት ነው፡፡ ምርጫ መተኪያ የሌላቸውን የዲሞክራሲ እሴቶችን እየገነባን የምንራመድበት ሂደት ነው፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢሕአዴግ ራሱን ለማሻሻልና ቀደም ሲል ከነበረበት የማን አለብኝነት አስተሳሰብ ራሱን ለማጽዳት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ፣ በአገራችን ምርጫ እስካለ ድረስ ሕዝብ አንቅሮ የሚተፋበት ሁኔታ በገሃድ የሚረጋገጥበት አጋጣሚ እንዳለ በግንቦቱ ምርጫ መረዳት ስለቻለ እንደሆነ ፓርቲያችን ይገነዘባል፡፡ በፓርቲያችን እምነት ይህ ሁልጊዜ መኖርና መቀጠል ያለበት ነው፡፡ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱንና ጉልበቱን የሚያሳይበት አንድ ወሳኝ ሂደት ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ምርጫ ነው፡፡

የእኛ የመጀመሪያ ትኩረት ይህ ዕድል ሳይቋረጥ እየሰፋና ሥር እየሰደደ የሚቀጥልበትን ሂደት መፍጠር ነው፡፡ ይህ ሂደት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ወሳኝ የሆኑ መሠረቶችን እየገነቡ ለመቀጠል ያስችላል፡፡ ከአንድ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚጠበቀው የመጨረሻ ውጤት ማለትም ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር እውን አልሆነም ብሎ ምርጫን ማጥላላትና ከምርጫ ማፈግፈግ ስህተት ነው፡፡ ይህንን ስንል የምርጫ ዋነኛ የምርጫ ውጤት የሆነው ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር እውን ሳይሆን መቋጫ በሌለው መዳከር ውስጥ እንቀጥል እያልን አይደለም፡፡ ከዚህ መዳከር ለመውጣትና መልካሙን ውጤት በተቻለ መጠን በቅርብ እንድናጣጥመው ከተፈለገ ትግላችንን የግድ ቀጣይ ማድረግ ያስፈልገናል፣ በአንድ ጊዜ ውድቀት ተስፋ ሳንቆርጥ የትናንትናውን ስህተት ለዛሬ እርምጃችንና ለነገ መንገዳችን ትምህርት እያደረግን እንቀጥል ማለታችን ነው፡፡

በዚህ መንፈስና ሐሳብ ፓርቲያችን በመጪው ሚያዚያ ወር በሚደረገው የቀበሌና ወረዳ ምርጫ በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ሆኖ አቅሙና ወቅታዊ ሁኔታው በፈቀደለት መጠን ለመሳተፍ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ግለሰቦችን በመጥላትና ትግሉን በመጉዳት መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ በተሳናቸው ግለሰቦች በፓርቲያችን ላይ በተካሄደው ከፍተኛ የአሉባልታ ዘመቻ ፓርቲያችን በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት አጋጥሞታል፡፡ ከላይ በገለፅነው የቅንጅት መሪዎች የስልት ስህተትና በገኘው ፓርቲ መጠን ያለፈ የአፈና ድርጊት ምክኒያት ደጋፊዎቻችን በምርጫ ላይ ያላቸው እምነት በጣም ከመጐዳቱም በላይ የፓርቲ የምርጫ ዕጩ ሆኖ መቅረብም በዚያው መጠን የአባሎቻችንን ሞራል የሚፈታተን ሆኗል፡፡ ነገር ግን ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን የፖለቲካው አየር በተሟሟቀበት አመቺ ወቅት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ተስፋ መቁረጥና መዳከም በተፈጠረበትም አስቸጋሪ ወቅት ሕዝቡንና የትግሉን ሂደት ከድቶ የማይሸሽ በመሆኑ በምርጫው ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ ይህ ተሳትፎውም ምርጫን ከማሸነፍና ከመሸነፍ በላይ ፓርቲው ለራሱ መርህና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት መገንባት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ኢዴአፓ-መድህንን በሁለንተናዊ መልኩ መደገፍ፣ ኢዴአፓ-መድህንን ከመጥቀም ያለፈ አገራዊ ትርጉም ያለው ቁም ነገር ነው ብለን እናምናለን፡፡ ስለሆነም የፖለቲካ መስመራችንን ትክክለኛነት የተረዳችሁ ዜጐች ሁሉ በሃሣብ፣ በገንዘብና በልዩ ልዩ ተሣትፎዎች አቅማችሁ የፈቀደውን እገዛ ታደርጉለት ዘንድ ፓርቲያችን ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

ሠላምና ሕብረ-ብሔራዊነት ዓላማችን ነው!
የኢዴአፓ-መድህን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
የካቲት 2000
አዲስ አበባ



☏ 0115-508727 0114655765 ✉ 101458
0115-508728
ፍልውሃ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር A/C 145